## መርህ ሁለት

## ቁርአንና የመልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ሱና የህግ ምንጮች ናቸው




- «የተከበረው ቁርአን እና የነቢዩ ሱና እያንዳንዱ ሙስሊም የኃይማኖቱን ህግጋት ለማወቅ መነሻ የሚያደርጋቸው ዋቢዎች ናቸው። የተከበረውን የቁርአን መልዕክት በዐረብኛ ቋንቋ መርሆች ላይ በመመስረት ይረዳዋል። ቃላቱ መሸከም ከሚችሉት በላይ የሆነ ትርጉም በማስሸከም ራሱን አያስጨንቅም። ያለ ዕውቀት፣ ከመመሪያ ውጭ በሆነ እንዝህላልነትም የተሸከሙትን ትርጉማቸውን አይሰለብም። የንፁሁን ሱናን መልዕክት ለመረዳት ደግሞ ታማኝ ወደሆኑ የሐዲስ ልሂቃን ሃሳብ ይመለሳል።

ዓብዱራህማን ሰዒድ(ሜጢ)
1441 ዓ.ሂ

## ማብራሪያ

ሰማዕቱ መሪ ለሁሉም ሙስሊም የድንጋጌ ምንጭ ሊሆን ብቃቱ ያለው ቁርአንና ሱና መሆኑን በሚገባ አብራርተዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ መረጃዎችን መግለጽ ይቻላል፡-

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا أَطِيعُوا اللَّهَ وَأَطِيعُوا الرَّسُولَ وَأُولِي الْأَمْرِ مِنكُمْ ۖ فَإِن تَنَازَعْتُمْ فِي شَيْءٍ فَرُدُّوهُ إِلَى اللَّهِ وَالرَّسُولِ

*‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገዙ። መልክተኛውንና ከእናንተም የስልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ። በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ብትኾኑ (የተከራከራችሁበትን ነገር) ወደ አላህና ወደ መልክተኛው መልሱት።›› (ኒሳእ፡59)*

وَنَزَّلْنَا عَلَيْكَ الْكِتَابَ تِبْيَانًا لِّكُلِّ شَيْءٍ وَهُدًى وَرَحْمَةً وَبُشْرَىٰ لِلْمُسْلِمِينَ

*‹‹መጽሐፉንም ለሁሉ ነገር አብራሪ፣ መሪም፣ እዝነትም፣ ለሙስሊሞችም አብሳሪ ኾኖ ባንተ ላይ አወረድነው።››(ነህል፡89)*

إِنَّ هَٰذَا الْقُرْآنَ يَهْدِي لِلَّتِي هِيَ أَقْوَمُ

*‹‹ይህ ቁርኣን ወደዚያች እርሷ ቀጥተኛ ወደ ኾነችው መንገድ ይመራል።››(ኢስራእ፣9)*

وَمَا آتَاكُمُ الرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَاكُمْ عَنْهُ فَانتَهُوا

*‹‹መልክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት። ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ።››(ሀሽር፡7)*

ቁርአን የኢስላማዊ ህግጋት እና ብያኔዎች የመጀመሪያው ምንጭ እንዲሁም ማስረጃ ለመሆኑ በሙስሊሞች መሃል ፍፁም ልዩነት የለም። ሱና ደግሞ ደግሞ የቁርአን ማሟያ እና ማብራሪያው ስለሆነ ልክ እንደ ቁርአን እርሱንም መከተሉ ግዴታ ነው። ሁለቱም የአላህ ራዕዮች ናቸው። ቁርአን ቃላቱም ይሁን የትርጉም መልዕክቱ መለኮታዊ ራዕይ ነው። ሱና ግን መልዕክቱ ከአላህ ሲሆን ቃላቱ ከተከበሩት ነብይ ነው።

ቁርአን ግልፅ በሆነው የዐረብኛ ቋንቋ ስለወረደ ከአናቅፁ ህግጋትን ለማወቅ የቋንቋውን መርሆችና የገለፃ ዘዬ ማወቅ ያስፈልጋል። ብያኔዎችን ለማወቅ ደግሞ ናሲኽ እና መንሱኽ፣ አንቀፁ የወረደበትን ሰበብ(ሰበበ-ን-ኑዙል)፣ የብያኔው ጥበብ ወዘተ እና  ሌሎች የቁርአን ጥናት ዘርፎችን ማወቅ ያሻል። በተጨማሪም የቁርአናዊ አናቅፁ ምን እንደተፈለገባቸው ለመገንዘብ የነብያዊ ሐዲሶች የተነገሩበትንም ብያኔ ማወቅ ያስፈልጋል።

ይህ ሁኔታ ግን ሁሉም ሙስሊሞች ዘንድ አንድ ዓይነት አይደለም። ሁሉም ቁርአንን በቻለውና በሚያውቀው መጠን ይረዳዋል። ከቁርአን ምንም መረዳት ያልቻለ ደግሞ ወደ አዋቂ በመሄድ ይገነዘባል፣ይማራል።

የነብያዊውን ሱና(ሐዲስ) ማወቅ ደግሞ ሰነድ እና ዋና ቴክስቱን(መትን) ማወቅ ላይ ያተኩራል። ***ሰነድ*** ስንል ለሐዲሱ ተዓማኒነት የዘጋቢያኑን ማንነት የምናውቅበት ሂደታዊ ፍተሻ ነው። አንድ ሙስሊም የአንድን ሐዲስ ትክክለኛነት ለማወቅ ከፈለገ የመስኩ ምሁራን ያስቀመጧቸውን ሳይንሶች መማር (ጀርሕ-ወ- ተዕዲል) ይኖርበታል። ምሁራኑ ትክክለኛ ሐዲሶችን በተለየ ሰነድ ሰድረዋል። ሌሎች ደግሞ የተቀጠፉና ደካማ ሰነድ ያላቸውን ሰብስበዋል። አንድ ሰው እነኚህን ልዩነቶች ካጤነና የማንበቡን ዕድል ካገኘ አስተማማኝ የሆኑትን እንዲሁም የሚሰራባቸውን ሐዲሶች ያውቃል ማለት ነው። የትክክለኛ ሐዲሶቹ ድርሳናት ሶሒሕ አል-ቡኻሪ፣ሶሒሕ ሙስሊም፣ ሱነን አቢ ዳውድ፣ቲርሚዚ፣ነሳኢ እና ኢብኑ ማጃህ ናቸው።

የዕውቀት ባለቤቶች ሶሒሕ አል-ቡኻሪ ከአላህ መፅሐፍ ቀጥሎ በትክክለኝነቱ እምነት የሚጣልበት ድርሳን እንደሆነ፣ቀጥሎ ደግሞ ሶሒሕ ሙስሊም፣ ከዚያም ደግሞ ሌሎች የተጠቀሱት አራቱ ናቸው። የቡኻሪና ሙስሊም ሐዲሶች ዘጋቢዎች ትክክል ስለሆኑ አንድ ሙስሊም በልበ ሙሉነት አምኖና ተቀብሎ ይሰራባቸዋል።

**መትን ወይም ዋናውን ቴክስት ማወቅ**፡- ከቃላትና ትርጉም ጀምሮ ሐዲሱ የያዛቸውን ህግጋት ማወቅ ነው። አንድ ሙስሊም በዘርፉ የዳበረ ዕውቀት እንዲኖረው ለመረዳት ደግሞ ወደ ሐዲስ ልሂቃን ይመለሳል፣ከስራቸው ሆኖም ይማራል።

*ዓብዱራህማን ሰዒድ(ሜጢ)*

*ረመዷን 1441*